# በግልፅ አጀንዳ በግልፅ አካሄድ!!!

የኢትዮጵያ ህዝብ በግንቦት 97 የምርጫ ሂደት ታግሎና ተሰውቶ የተጎናፀፋቸውን ድሎች ጥቂት የስልጣን ጥመኞች አይን ባወጣ መልክ ቢቀሙትም ይህንን የልጆቹን ክቡር መስዋእትነት ፍሬ መልሶ እጁ ለማስገባት ካስፈለገ ተጨማሪ መስዋእትነት እየከፈልኩም ቢሆን ተጋድሎየን እቀጥላለሁ ታግላችሁ አታግሉኝ እያለ ሲወተውት ወራት አስቆጥሩዋል። ይህንን ህዝባዊ ጥሪ እውን ለማድረግና ሃገራችን የተያያዛችው የዴሞክራሲ፤ የሰላምና የብሄራዊ እ-ርቅ ሂደት ፈር ስቶ መልሰን አንቅረን ወደተፋነው የአፈና፤ የግፍና የቂም በቀል አዙሪት እንዳንዘፈቅ ህብረታችንና ቅንጅቱ ይህንን የህዝብ ጥሪ ሰምተው ለዚህ ተጋድሎ ተፈላጊውን አመራር ለመስጠት የማይታጠፍ ቃላቸውን በሰጡት መሰረት እስካሁን እየታገሉ ሲያታግሉት ቆይተዋል። ሆኖም ጥቂት የኢህአዴግ መሪዎች ለዚህ የህዝብ የማያወላውል ፈቃድ ከመገዛት ይልቅ ለዚህ ሰማእትና ታጋይ ህዝብ ያላቸውን ከፍተኛ ንቀት ባጋለጠባቸው መልክ ከራሳቸው ህገ መንግስት አንፃር እንኳዋን ጨርሶ ህገ ወጥ የሆነ የሌቦች ዋሻ ፓርላሜንታቸውን መስርተው፤ በዚህ ከጥንስሱ ህገ ወጥ በመሆኑ መንግስት ለመመስረት ህገ መንግስታዊም፤ ፖለቲካዊም፤ ህጋዊም ሆነ የሞራል ብቃት በሌለው ፓርላማ መንግስት ሰየምን ብለው ሃገራችንን ለሌላ አምስት አመት የግፍ አገዛዝ እያመቻቹ ይገኛሉ።

በህብረታችን እምነት እነዚህ ጥቂቶች በዚህ ህገ ወጥ ጎዳና እንዲቀጥሉ ፈቅደንላቸው ከቀጠሉና የህዝባችን ትግል ትጥቅ ከፈታ ግፈኛ አገዛዛቸው በሃገራች-ን ላይ የመከራ ዘመኑን የሚያራዝመው ለቀጣዮቹ አምስት አመታት ብቻ አይሆንም። ይህ ዛሬ በአይናችን ስር ተቀጣጥሎ የህዝባችንን ድል ለማስከበር የሚካሄደው ተጋድሎ በጥቂት ስልጣን ጥመኞች አመፅ ከተሸነፈና እኛም ዛሬ ይህንን አመፅ በሰላማዊና ህዝባዊ ክንድ ተቋዋቁመን ወደ ፊት ካልተራመድን የዛሬ አምስት አመትም፤ የዛሬ አስር አመትም ተንቀሳቅሰን ህዝባችን ድል ቢያደርግ እንኳዋን እንደገና በአመፅ ድሉን ሳለመቀማቱ ም-ንም ዋስትና ስለማይኖር ሃገራችን አስርም ሃያም አመት ወደኋላ ተጉዛ የመከራውና የግፉ ዘመን ለረጅም ጊዜ እንደሚቀጥል ለሁላችንም ግል-ፅ መሆን ይኖርበታል።

በመሆኑም ከእንግዲህ ለህዝባችን የሞት ሽረት የሆነው የግንቦት ድሎች መከበር ጉዳይ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የማንም የማንም ሳይሆን የህዝባችን ጉዳይ በመሆኑና ህዝባችንም በዋና ባለጉዳይነት "ያገባኛል ልግባበት" እያለ የሚያስተጋባውን የምሩኝ ልከተላችሁ ጥሪ እኛ ታጋይ ሃይሎች ሰምተን ለዚህ ሁኔታዎችን ስናመቻች ቆይተናል። በተደጋጋሚ ከህዝባችንም፤ ከየድር-ጅቶቻችን አባላትና ደጋፊዎችም፤ ከጠቅላላው በውጭም በውስጥም ካሉ ዴሞክራቶችና አገር ወዳዶችም የሚያስተጋባውን ጥሪ በማዳመጥ የቅን-ጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ አመራር ከጥቅምት 19 ቀን ጀምሮ በተከታታይ የሚደረጉ የሰላማዊ ተጋድሎ ስልቶች በዝርዝር አቅርቦ ከዚህ በተጨማሪ ከህዳር 5 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ የቤት መዋል አድማ እንዲካሄድ ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ ጥሪ አስተላልፉዋል። ህብረታችን በተለይ ከሶስት ሳምንታት ወዲህ "ዜጎች ለግንቦት ድሎች" እንሰባሰብ በሚል ጥሪ ህዝባች-ን ከትግሉ በአንድነት ሆኖ፤ በአንድ መንፈስና በአንድ ወኔ የተሰረቀ ድሉን ለማስከበር እንዲንቀሳቀስ ጥሪ ሲያደርግ የቆየበት ጉዳይ በመሆኑ ይህንን ጥሪ ይደግፋል። በውስጥም በውጭም ያሉ አባላቱና ደጋፊዎቹ እንደዚሁም መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ይህ የትግል ጥሪ የህብረቱም የቅንጅቱም ሳይሆን ከራሳቸው ፍላጎትና ፈቃድ የመነጨ ጥሪ አድርገው በመቁጠር ለተግባራዊነቱ ከዳር እስከዳር እንዲንቀሳቀሱና ጥቂት የኢህአዴግ መሪዎችና አንዳን-ድ ባእዳን የተዘጋ የመሰላቸው የግንቦት ምእራፍ ከመዘጋት ይል-ቅ ወደ ሌላ ከፍተኛ የትግል ምእራፍ እየተሸጋገረ መሆኑን እንዲያሳዩ ሃገራዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ህዝባችንን ይዘንና በህዝባችን ታቅፈን የምንያያዘው አዲስ የትግል ምእራፍ አላማውና ስልቱ ግል-ፅ ነው። ህዝባችን በዚህ አዲስ ምእራፍ የሚጠበቅበትን መስዋእትነት ለመክፈል ቆርጦ የሚነሳሳው የተነጠቁ የግንቦት ድሎቹን መልሶ እጁ ለማስገባት ነው። ይህንን የሚያደርገው ደግሞ ወይ በአጠቃላይ የግንቦቱ ምርጫ ሂደት በአዲስ መልክ በተዋቀረ ሁሉም ወገን በተስማሙበት ገለልተኛ አካል ሲገመገም ወይ ደግሞ ሌላው ቀርቶ አለም አቀፍ ኮሙኒቲውም ለመጭበርበሩ የምስክር ቃል የሰጠበት ምርጫ በሌላና ሁሉም በተስማማበት የም-ርጫ ቦርድ፤ በሌላና ዴሞክራሲ በሰፈነበት አካባቢ ሲደገም ብቻ ነው። ሳለፉት ስድስት ወራት የኢህአዴግን መሪዎች የህዝብ ድም-ፅ

አክብሩ እያልን ስንጮህ እኛ የህዝብ ድም-ፅ አለማዳመጣችን የማይታሰብ ጉዳይ ስለሆነ፤ የኢህአዴግ መሪዎችን ላለፉት ስድስት ወራት የፈሰሰውን የልጆቻችንን ደምና የወላጅ እንባ እንደ ቀጭን ውሃ ቆጥራችሁ አታዋርዱት እያልን እየተሟገትናቸው እኛ "የህዝብ ድምፅ ይከበር" እያሉ የወደቁትን ዜጎች ሰማእትነት አለማክበራችን የማይታሰም ጉዳይ በመሆኑ፤ የኢህአዴግ መሪዎች በውጭም በውስጥም የህዝብ ድምፅ ይከበር ብለው ስፍር ቁጥር የሌላቸው ዜጎች የሚያካሂዱትን ተጋድሎ ሚዛን የማይደፋና የትም የማያደርስ የጥቂቶች መፍጨርጨር አድርገው ሲንቁት እኛ ለዚህ ህዝባዊ ማእበል ጆሮ ዳባ ልበስ የም-ንልበት የታጋዮች ንቀት ባህል ስለሌለን ከዚህ የህዝብ ድምፅ ከማስከበር በመለስ የምንረካበት ምንም አይነት ድል እንደማይኖር ለሚመለከተው ሁሉ ከወዲሁ ግልፅ መሆን ይኖርበታል።

የትግል ስልታችንም ከዚህ ዘላቂና ህዝባዊ አላማ ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው። አላማችን የኢህአዴግ መሪዎች የህዝቡ ድምፅ ስለሚከበርበት ሁኔታ ትርጉም ወዳለው ድርድር እንዲመጡና ለኛም ለነሱም ለህዝባችንም የሚበጅ ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ ላይ ለመድረስ ነው። ከዚህ በመለስ የምንደራደርበት ጉዳይ ሊኖር አይችልም። በህዝብና በአለም አቀፉ ኮሙኒቲ ግፊት የድ-ርድርን ሃሳብ ከተቀበሉ መጀመሪያ ነገር የድርድሩ አጀንዳ በቅድሚያ ለህዝብና በሃገሪቱ ላሉ ዴሞክራሲያዊና ሃገር ወዳድ ሃይሎች በሙሉ በግልፅና በይፋ መቀመጥ ይኖርበታል። ሁለተኛ ነገር ይህ የድርድር ጥሪ ወይም ፍላጎት የህ-ዝባችንን ትግልና እንቅስቃሴ የሚተካ መሆን የለበትም። የፀረ ህዝብ ተንኮል ቋት የሆኑት የኢህአዴግ መሪዎች ሲያመቻቸው በአመፅ ሳያመቻቸው በመለሳለስ የህዝቡን ትግል ለማደናገርና ለማሰናከል ስለማይመለሱ ከወዲሁ አንድ ነገር ግል-ፅ ሆኖ መቀመጥ ይኖርበታል። ከእንግዲህ ማንኛውም ድርድር ህብረተሰቡን ከዳር እስከዳር አንቀሳቅሶ፤ ህ-ዝባችን ከመሪዎቻችን ጀርባ በተጠንቀቅ ቆሞ ብቻ መደረግ ስለሚኖርበት የተጠራውና እኛም የኢትዮድያ ህዝብም በሙሉ ልብ የምንደግፈው የቤት መዋል አድማ በምንም መልክና ሰበብ እንደገና መሰረዝ እንደሌለበት በግልፅ መታወቅ ይኖርበታል።

የኢትዮድያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህብረት ከነዚህ ነጥቦች በመነሳትና ለነዚህ አላማዎች መሳካት ህዝባችን ከዳር እስከዳር እንደ አን-ድ ሰው ሆኖ እንዲነሳ ጥሪ እያደረገ በውጭ የሚገኙ የህዝባችንን ድምፅ ለማስከበር በመዋደቅ ላይ የሚገኙ ስብስቦችም አንደኛ በዚህ ጥሪና በሚከተለው እንቅሳቃሴ ሳቢያ የኢህአዴግ መሪዎች በህዝባችንና በመሪዎቻችን ላይ ም-ንም አይነት የሃይል እርምጃ ቢወስዱ ለአመፀኛው አገዛዝ ም-ንም ፋታ በማይሰጥ ሁኔታ በሰላማዊ ሰልፎችና በሌሎች የትግል ስልቶች አማካኝነት ለመንቀሳቀስ በተጠንቀቅ እንዲጠብቁ፤ ሁለተኛ የቤት መዋሉ አድማ በሚጀመርበት ህዳር አምስት ለመላው አለም የህዝባችን ትግል ህያው መሆኑን ለማሳየት በተለይ በዋና ዋና የአለም ከተሞች ሰላማዊ ሰልፍ እንዲያዘጋጁ ሶስተኛ መጭው ውስብስብ ትግል በሃገር ውስጥ ለሚዋደቁ ዜጎች ከባድ የገንዘብና የማቴርያል ጥረት ስለሚጠይቅ በያለበት በተቋቋሙ የድጋፍ ኮሚቴዎች አማካኝነት የገንዘብ ስብሰባ ዘመቻ እንዲያካሂዱ ጥሪ እያቀረብን በያለበት የሚገኙ የህብረታችን አባላት፤ ደጋፊዎችና የድጋፍ ኮሚቴዎች ለዚህ የጋራ ትግል መሳካት የሚያደርጉትን ጥረት ከእስካሁኑ እጥፍ ድርብ በማድረግ "የግንቦት ምእራፍ አልተዘጋም አይዘጋምም" ብለን ሳስተላለፍነው ጥሪ እ-ውንነት እንዲዋደቁ ሃገራዊ ጥሪያች-ንን ከአክብሮት ጋር እናስተላልፍላዋለን።

የግንቦት ድሎች በዜጎች የጋራ ተጋድሎ ይከበራሉ
የኢትዮድያ ዴሞክራሲያዊ ሃይሎች ህ-ብረት
ጥቅምት 21 ቀን 1998 ዓ.ም.